LHL Internasjonal

**LHLs internasjonale tuberkulosestiftelse**
Adresse: Grensen 3, 7. etasje, 0159 OSLO
Telefon: 22 79 92 22
post@lhl-internasjonal.no
www.lhl-internasjonal.no
Giverkonto: 1503 33 09462

folkehelseinstituttet

**Nasjonalt folkehelseinstitutt**
Postboks 4404 Nydalen
0403 Oslo
Telefon: 21 07 70 00

**Oslo kommune**
Utdanningsetaten
Oslo Voksenopplæring



# ከ ቲዩበርክሎሰሰ (ከሳንባ ነቀርሳ)

## ትድናላችሁ



## ቲቢ የሚይዘው ማን ነው?

በሁሉም ሃገሮች ቲቢ ያለባቸው ሰዎች አሉ። ቲቢ በእስያ፣ አፍሪካ፣ ላቲን አሜሪካ እና በምስራቅ አውሮፓ በአብዛኛው የተለመደ አይደለም፤ ስለሆነም፣ ብዙውን ጊዜ በባክቴሪያው የሚያዙት እና የሚታመሙት ከእነኝህ የአለም ክፍል የመጡ ሰዎች ናቸው።

ቲቢ በአብኣኛው የተለመደ በሽታ ከሆነበት ሃገር የሚመጡ ሰዎች ሁሉ ኖርዌይ በደረሱ በአጭር ቀናት ውስጥ የቲቢ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ምርመራዎ እርስዎ በሚኖሩበት ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ባለ የጤና ባለሞያ አማካኝነት የሚደረግ ይሆናል።

## በርካታ ሰዎች ለምንድን ነው ቲቢን የሚፈሩት?

ሰዎች ቲቢን የሚፈሩበት ምክንያት ብዙውን ጊዜ ስለ በሽታው በቂ የሆነ መረጃ ስለማይኖራቸው ወይም ስለማያውቁ ነው። በቂ እውቀት የሌላቸው ሰዎች በራሳቸው አመለካከት ላይ ይደገፋሉ ወይም የራሳቸው የሆነ ማብራሪያን ይሰጣሉ። ለምሳሌ፣ በርካታ ሰዎች፣ በቲቢ እንዳይያዙ ይፈራሉ ምክንያቱም በየእለቱ መድሃኒት የሚወስዱ የቲቢ በሽተኞች ለሌሎች ሰዎች በሽታውን እንደማያስተላልፉ አያውቁም።

ስለዚህም፣ በርካታ የቲቢ በሽተኞች ይፈራሉ እንዲሁም በሽታቸውን ሌሎች ሰዎች እንዳያውቁባቸው ይደብቃሉ። ሰዎች የቲቢ በሽተኞች እንደሆኑ ካወቁባቸው ከእነርሱ እንዳይሸሹ፣ አብረዋቸው ለመመገብ አንቢ እንዳይሉ፣ እና የመሳሰሉትን ይፈራሉ። የቲቢ ምልክቶች ያለባቸው ሰዎችም አንዳንድ ጊዜ ይህንን ሁኔታ ይፈራሉ፣ እና ይህ ፍርሃት ዶክተርን ከመጎብኘት እና ስቃያቸው ከምን የመነጨ እንደሆነ ከማወቅ ያግዳቸዋል።

ሰዎች ስለ ቲቢ እውቀት ሲኖራቸው እና የቲቢ በሽተኞች ውጤታማ የሆነ የቲቢ መድሃኒት በሚወስዱበት ጊዜ ሌሎችን እንደማይበክሉ በሚያውቁበት ጊዜ፣ ደህንነት ይሰማቸዋል። እንዲሁም ደግሞ የቲቢ በሽተኛ ለሆነ ሰው የተሻለ እክብካቤ እና ድጋፍ ለመስጠትም ይችላሉ።

ስለ ቲቢ የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ? የኖርዌይ የህዝብ ጤና ማዕከልን / Folkehelseinstituttet (www.fhi.no) ወይም LHL Internasjonal (www.lhl-internasjonal.no) ድህረ ገጽ ይጎብኙ።

በድህረ ገጽ www.lhl-internasjonal.no የዚህን በራሪ ወረቀት ሰፋ ያለ ቅጂ በተለያየ ቋንቋ ማግኘት ይችላሉ።

## ሣንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) በባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው። ባክቴሪያ ጥቃቅን እና የማይታዩ ሕዋሳት ናቸው እንዲሁም ደግሞ በማንኛውም ስፍራ የሚገኙ ሲሆን በሰውነታችን ውስጥም ይገኛሉ። አብዛኞቹ ባክቴሪያዎች አደገኛ አይደሉም፣ እንዲያውም ጠቃሚዎች ናቸው። ሆኖም ግን ጥቂት ባክቴሪያዎች አደገኛ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ኢንፌክሽን ብለን ለምንጠራቸው በሽታዎች ያጋልጡናል። ሳንባ ነቀርሳን የሚያመጡት እንደነዚህ አይነት ባክቴሪያዎች ናቸው። ባክቴሪያዎቹ በየትኛውም የሰውነታችን አካል ላይ ካረፉ፣ እራሳቸውን ካባዙ እና ሰውነታችን እራሱን መከላከል ካልቻለ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ሊይዘን ይችላል።

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በሳንባ ውስጥ መገኙቱ የተለመደ ሲሆን፣ ነገር ግን አንዳንዴ በሌላ የሰውነት አካልም ሊገኝ ይችላል (ለምሳሌ በአጥንት ላይ፣ በነጭ የደም ሴል ማጣሪያዎች ወይም በህብለሰረሰር እና በአንጎል ውስጥ)።

- ቲቢ በህክምና የሚድን በሽታ ነው
- በኖርዌይ ውስጥ ለሚቆይ (ለሚኖር) ለማንኛውም ሰው የቲቢ በሽታ መድኃኒት በነፃ ይሰጣል


## ቲቢን እንዴት ማከም ይቻላል?

ቲቢ በመድሃኒት ነው የሚታከመው፣ በአብዛኛው በእንክብል (በኪኒን)። በኖርዌይ ውስጥ እነኝህ መድሃኒቶች ከክፍያ ነፃ ናቸው። አብዛኞቹ የቲቢ በሽታ ህመምተኞች መድሃኒቱን ለስድስት ወራት በየቀኑ መውሰድ ይኖርባቸዋል ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ ህክምናው ከዚህ የበለጠ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። በአብዛኛው፣ የጤና ባለሞያ በየእለቱ ወደ እርስዎ እየመጣ መድሃኒቱን ይሰጥዎታል። ህክምናውን ከጨረሱ በኋላ፣ ከሳንባ ነቀርሳ/ቲቢ በሽታ ይፈወሳሉ።

Brosjyren er utgitt av LHL Internasjonal og Folkehelseinstituttet

## በቲቢ ሊያዙ የሚችሉት እንዴት ነው?

ቲቢ አየር ውስጥ ባሉ ጥቃቅን ህዋሳት (በአይን ሊታዩ በማይችሉ) ይሰራጫል። ጥቃቅን ህዋሳቱ በቲቢ በሽታ ከተያዘ ሰው አፍንጫ እና አፍ የሚወጡ ሲሆኑ በበሽታው የተያዘ ሰው በሚያስልበት፣ በሚያስነጥስበት ጊዜ እና በሚያወራበት ጊዜ በአየር ላይ ይሰራጫሉ። የቲቢ ባክቴሪያዎች በእነኝህ ህዋሳቶች ውስጥ ይገኛሉ። ጤነኛ የሆነ ሰው በነዚህ ህዋሳት የተበከለ አየር ሲተነፍስ ህዋሳቱ ወደ ሰውየው ሰውነት በመግባት ሳንባው ጋር ሊደርሱ ይችላሉ።

የቲቢ ባክቴሪያ በቀላሉ አይሰራጭም፣ ስለሆነም በአብዛኛው በአንድ ላይ (አብረው) በሚኖሩ ሰዎች መካከል ይከሰታል። የሳንባ ነቀርሳ/ቲቢ እና በአብዛኛው የማይታይ (የማይከሰት) የጉሮሮ ቲቢ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፉ የሚችሉት በዚህ መንገድ ነው። ከ2–3 ሳምንት የቲቢ መድሃኒት በአግባቡ የወሰደ ሰው በሽታውን ሊያስተላልፍብዎ አይችልም።

## በበሽታው ከተያዙ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ይታመማሉ

**የቲቢ ባክቴሪያ ያላቸው ሰዎች ህመም ላይኖራቸው ይችላል።** በዓለም ላይ ከሚኖሩት ወደ 1/3 (አንደ ሶስተኛ) የሚሆኑት ህዝቦች የቲቢ ባክቴሪያ በሰውነታቸው ውስጥ የተሸከሙ ሲሆን፣ ሆኖም ግን ጥቂቶቹ ብቻ በሽታው ያጠቃቸዋል። በባክቴሪያው ከተያዙት ሰዎች ጥቂቶቹ ብቻ የሚታመሙበት ምክንያት ሰውነታቸው ዝቅተኛ የሆነ በሽታን የመከላከል አቅም (ሀይል) ስላለው ነው።

ዝቅተኛ የሆነ በሽታን የመከላከል አቅም የሚመጣው በሌሎች በሽታዎች ከመጠቃት፣ ከጭንቀት፣ ከአየር መለወጥ፣ ያልተመጣጠነ ምግብ ከመመገብ፣ አመጋገብን ከመቀየር፣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች አማካኝነት ነው። አንድ ሰው በባክቴሪያው ከተያዘ ከአመታት በኋላ ሊታመም ይችላል።

በባክቴሪያው ከተያዙ፣ ሆኖም ግን ካልታመሙ፣ ዶክተሩ ጥቂት የቲቢ መድሃኒቶች እንዲወስዱ ሊመክርዎት ይችላል (በአብዛኛው ለሶስት ወይም ለስድስት ወር) ይህም የሚደረገው ወደፊት እንዳይታመሙ ለመከላከል ነው። እንደዚህ ያለው ህክምና የቲቢ መከላከያ ህክምና ይባላል። ይህ ህክምና በፍቃደኝነት የሚደረግ ነው። **የቲቢ መከላከያ ህክምና ያደረጉ ሰዎች አይታመሙም እንዲሁም ደግሞ ሌሎችን አይበክሉም።**

## ቲቢ እንዳለብዎት እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ?

አንድ ሰው ከ2–3 ሳምንታት የሚያስለው ከሆነ በሳንባው ውስጥ ቲቢ ሊኖረው ይችላል። የሳንባ ነቀርሳ/ቲቢ ዋና ዋና ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- ከሳንባ ውስጥ የሚወጣ አክታ ያለው ሳል በሚኖርበት ጊዜ እና አንዳንድ ጊዜም አክታው ከደም ጋር የተቀላቀለ ሲሆን
- በደረት ላይ ህምም ሲሰማ


ማሳል

ሌሎች የተለመዱ የቲቢ ምልክቶች – ሁለቱም የሳንባ ቲቢ እና በሌሎች የሰውነት አካላት ላይ የሚኖር ቲቢ ፤


የምግብ ፍላጎት መቀነስ

ክብደት መቀነስ


የድካም ስሜት


ለተወሰነ ጊዜ ትኩሳት መኖር


ሌሊት ማላብ


በአንገት፣ ብብት፣ እና ብሽሽት ማበጥ

እነኝህ የሌሎች በሽታዎች የተለመዱ ምልክቶች ናቸው። ስለዚህም ቲቢ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን፣ የተለያዩ ምርመራዎችን ማድረግ ይኖርብዎታል። ከእነኝህ ምልክቶች አንዱ ወይም ከዛበላይ ያለው ማንኛውም ሰው ዶክተር ጋር ሄዶ/ሄዳ መመርመር አለበት/ባት!

የቲቢ በሽታ ያለበት ሰው በአብዛኛው እነኝህ ሁሉ ምልክቶች አይታይበትም። አንዳንድ ሰዎች ቀለል ያሉ ምልክቶች ብቻ ይታይባቸዋል።

## ቲቢ እንዳለብዎት የሚጠረጥሩ ከሆነ ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

ቲቢ እንዳለብዎት የሚጠረጥሩ ከሆነ፣ በተቻለ ፍጥነት ዶክተርዎን ፣ የድንገተኛ ክፍል (legevakten) ወይም በሚኖሩበት ማህበረሰብ (አካባቢ) ውስጥ ያለ የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ መጎብኘት አለብዎ። ህክምና በወቅቱ ከተደረገልዎ፣ በፍጥነት ይድናሉ።

አንድ ሰው ቲቢ እንዳለበት ለማወቅ፣ በርካታ ምርመራዎች ሊደረጉ ይችላሉ። በአብዛኛው የተለመዱ ምርመራዎች የሳንባ ኤክስ ሬይ፣ የቆዳ ምርመራ (ማንቶክስ የሚባለው)፣ እና/ወይም የደም ምርመራ ናቸው። የምርመራዎቹ ውጤቶች በቲቢ ባክቴሪያ እንደተያዙ የሚያሳዩ ከሆነ፣ በሆስፒታል ውስጥ ወደ አለ ስፔሻሊስት ሄደው እንዲታከሙ ይደረጋሉ።